# 5. የኮሚኒቲ የጤና ማእከሎች

## የሕዝብ የጤና አገልግሎቶች

እነዚህ አገልግሎቶች ጤና ለመጠበቅ፣ በሽታ፣ ጉዳት፣ እና ሕመምን ለመከላከል፣ እንዲሁም ጤንነትን ለመበረታታት ያለሙ ናቸው።

### አልኮሆል፡ ሥጋራ እና ሌሎች አደንዛዥ እጾች

- ሕክምና፣ ድጋፍ እና መረጃ እንዲሁም የመከላከያ ፕሮግራሞች

### የካንሰር ምርመራ አገልግሎቶች

- የጡት ካንሰር እና የሰርቪካል ካንሰር ምርመራ ፕሮግራሞች

### ጤንነት ማበረቻቻ ፕሮግራሞች

- የጤንነት ዋና አስፈላጊነትን የተመጣጠነ ምግብ፣ የአካል እንቅስቃሴ፣ ጉዳትን መከላከል እና የአሀይ ሙቀትና ደህንነትን ያጠቃለለ መግለጫ መስጠት፣ እና የጤንነትን ማበረታታት ፕሮግራሞች፣

### የአኗኗር ዘዴ መቆጣጠር ፕሮግራሞች

- ጤናማ የሆነ የአኗኗር ዘዴ ትምህርት እና የጤና አገልግሎቶች ስር በሰደዱ በሽታዎች እንዴት ለመቆጣጠር እንደሚቻል ያተኮረ ለምሳሌ፡ አርተሪስ፣ የስኳር በሽታ፣ የመተንፈሻ አካሎች፣ በጣም መወፈር፣ እና ኦስቶፖሮስን ያጠቃለለ

### ጾታዊ የጤና አገልግሎቶች

- ጾታዊ የጤና ክሊኒኮች፣ የሴቶች የጤና ነርሶች፣ እና የጾታ ጤና ትምህርት ፕሮግራሞች

## የጤና ፕሮግራሞች እና የድራግ ቡዱኖች

ብዙ የኮሚኒቲ የጤና ማእከሎች የተለየ በሽታ ላላቸው ሰዎች የድጋፍ ቡዱን እና ራስን የመርዳት ፕሮግራሞች ይሰጣል። ለምሳሌ፣

- አትተሪስ ራስን መደገፍ ፕሮግራም (Arthritis Self Help Program)
- የአስም ትምህርት ክፍሎች
- የካርዲአክ ማህበራዊ ኑሮ ፕሮግራም (Cardiac Rehabilitation Program)
- አንድ ወይም ሁለት የትምህርት ጊዜ ስለ ምግብ መስራት
- ጤናማ የሆነ ቤት በተመለከተ መረጃ
- ላይተን አፐ ፕሮግራም (Lighten Up Program) (ስለ መክሳት)
- የስኳር በሽታ የድጋፍ ቡዱን
- ወደ ሱፐር ማርኬት መሄድ።

የትኞቹ ብዱኖች እና ፕሮግራሞች እንደሚገኙ ለማወቅ፡ በአከባቢዎ የሚገኘውን የኮሚኒቲ የጤና ማእከልን ይጠይቁ።

## አስተርጓሚዎች

Interpreter

- የኩንስላንድ የህዝብ የጤና አገልግሎት በሚጠቀሙ ጊዜ የሚያስፈልግዎ ከሆነ፡ ፕሮፌሽናል የሆነ አስተርጓሚ የማግኘት መብት አልዎት
- እርስዎ ምንም ሳይከፍሉ አስተርጓሚዎች በአካል መጥተው ወይም ደግሞ በቴሌፎን በኩል ሊያስተረጉሙ ይችላሉ
- የኩንስላንድ የጤና ፖሊሲ በኢመርጀንሲ ሁኔታ ላይ ጓደኞች ወይም ቤተሰቦች ብቻ መገኘት እንዳለባቸው ይገልጻል። ጓደኛዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች ከሆነ፡ በምንም ዓይነት ሁኔታ እንደአስተርጓሚ ሆነው እንዲቀርቡ አይፈቀድም
- በቀጠሮዎ ቀን አስተርጓሚ እንዲላክልዎት፡ ፕሮፌሽናል የሆነ አስተርጓሚ እንደሚፈልጉ አባክዎን አስቀድመው ይጠይቁ

© QUEENSLAND HEALTH - JUNE 2007

ይህ መረጃ ጽሑፍ 10 ተከታታይ ክፍሎችን የያዘ ነው። በሙሉ ሲታይ፣


1፡ የጤና አጠባበቅ ዘዴ በኩንስላንድ
2፡ በሐኪም መታየት
3፡ መድሀኒቶች
4፡ የኩንስላንድ ሆስፒታሎች
5፡ የኮሚኒቲ የጤና ማእከላት
6፡ የጥርስ ሕክምና አገልግሎቶች
7፡ አላይድ (Allied) የጤና አገልግሎቶች
8፡ በጤንነት መኖር እና በሽታን መከላከል
9፡ ለተለዩ ብዱኖች የሚሰጥ የጤና እና የድጋፍ አገልግሎቶች
10፡ እርስዎ እና የጤና አገልግሎት ዘዴ ያካትታል።